# ጨለምተኞቹ "ጨለምተኛ" ሲሉ

ደመወዝ ክፍሉ

ትግራይ ኦንላይን May 23, 2014

የዚህ ፅሁፍ መነሻ የሰማያዊው ፖርቲ ልሣን የሆነው ነገረ ኢትዮጵያ ግንቦት 8 ቀን 2006 ዓ.ም እትሙ ልብ አድርጉ በሚለው የበላይ ማናዬ አምድ "የሥርዓቱ ክንድ የደቆሳቸው ማህበራት" በሚል የቀረበው ፅሁፍ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ግለሰቡ በቅርቡ ከመንግሥት ጋዜጠኝነት በቀጥታ የተቃዋሚ ፖርቲ ልሣን ምክትል ዋና አዘጋጅ ሆኖ ጋዜጣው ከተጀመረ አንስቶ ያቀረባቸው የተለያዩ መጣጥፎች በፍፁም ጥላቻ የተሞሉ፤ በስሜታዊነትና በጀብደኝነት የታጨቁ፤ ይፋ የአመጽ ጥሪዎችን፣ ሁከትና ደም መፋሰሶችን የሚጠሩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ዋናው ነጥብ ፅሁፉ በቂ ጭብጥ የሌለው በስማ በለው ያገኘውን ሳያጣራ በመፃፍ ለሕዝብ ለማስነበብ መጣደፉን ያሳያል፡፡ ማህበራቱንም በስም ለይቶ አያውቃቸውም፡፡ የአንድን ታሪክ ለሌላው በማውረስም መሠረታዊ ግድፈት ፈጽሟል፡፡ ከሞላና ከተረፈውም የአማርኛ ቋንቋ ፀያፉን በመምረጥ የጋዜጠኛ ማህበራቱን "የበከቱ" ብሏቸዋል በፅሁፉ፡፡

ስለዚህ በላይ ማናዬን የራሱን ቋንቋ ልዋስና የበከተ አስተሳሰቡን፤ የማይጨበጥ ሕልምና ምኞቱን እየዳከረበት ያለውን ዳፍንት አመለካከቱን ማሳየት ግድ ይላል፡፡

የአንድ ተቃዋሚ ፖርቲ ልሣን ምክትል ዋና አዘጋጅ ሆኖ ይህን አመለካከት ሲያራምድ ይህ የግለሰቡ ብቻ ሳይሆን የሰማያዊ ፖርቲን የጨቀየ አስተሳሰብና አቋም የሚያሳይም ጭምር ነው፡፡

ዳሩ ገና ዳዴ ሳይል ራሱን ያተበየው፤ ስለኢትዮጵያ ታሪክም ሆነ የትናንቱ ትውልድ የትግል ተሞክሮና መስዋዕትነት፤ ፈተና መከራና ውጣ ውረድ፤ ከድክመቱም ከጥንካሬውም አንድም ምንም ሳይማር፤ ከእኔ በላይ ለኢትዮጵያ አሳቢ፣ ተቆርቋሪ፣ ተሟጋች ማንም የለም ቁጥር አንዱ እኔ ነኝ የሚለው የኢንጂነር "ቾኮሉ" ሰማያዊ ፖርቲ፣ እምቡር...እምቡር ማለቱን ትቶ በስክነትና በማስተዋል ቢያስብ ለራሱም በበጀው ነበር፡፡

ደርሶ በእብጠት መወጠር፤ ከሁሉም ጋር መናቸፍ፣ እንደ አበደ ውሻ ያገኘሁትን ሁሉ ልናከስ ማለቱን ቢመርጠውም ግን ደግሞ የሚበጅ መንገድ አይደለምና የፈጣሪ አባቱን ልክፍትና ተሳዳቢነት ልጁ መውረሱ ብዙም አይገርምም፡፡ ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያምም አገር ያወቃቸው፣ ፀሐይ የሞቃቸው ነገረ ሰሪ ናቸውና፡፡

ሰማያዊ ፖርቲ ይህን ደም የወረሰው ሁሉን ማውገዝና መንቀፍ፤ አመጽና ብጥብጥን ከልብ ማፍቀር፤ ሲላቸውም ቦክስ ከሚጋጠሙት፤ በጡንቻና በአስገብር ፖለቲካ ከሚያምኑት ፈጣሪ አባቱ ኘሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም መሆኑን ሁሉም ያውቃል፡፡

የሚገርመው በዝምድናና በወንዝ ልጅነት እነ በላይ ማናዬ፣ እነ ፕሮፌሰር መሥፍንና ኢንጂነር ይልቃል መሰባሰባቸውና ማሰባሰባቸው ነው፡፡ ኢትዮጵያ እኮ ሰፊና ታላቅ ሀገር ነች፤ ምነው ጃል በኢትዮጵያዊነት ስም ባታደነቁሩን?

አባቱ ተሳዳቢ የሆነ ልጅ በማን ይወጣል ብለህ ነው በላይ ማናዬ? እንዲያ ለመሆኑ ሺህ አስረጂዎችን መንቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህ ነው የአንተና የፓርቲህም የአስተሳሰብ ምክነትና መዝቀጥ የሚነሳው።

የመጀመሪያው የአስተሳሰብ መውረድ ስለኢትዮጵያዊነት፣ ስለ ሀገር ፍቅር፣ ስለጀግንነት የቆማችሁ በማስመሰል ነገር ግን ሙሉ በሙሉ የውጭ ኃይሎችን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጐት ለማሳካት በኒዮ ሊበራል ኃይሎች እግር ሥር በመንበርከክ ሥልጣን ላይ አውጡን ብላችሁ ጫማቸው ሥር መንከባለላችሁ ነው፡፡

ኩሩውን አበሻ ጀግናውን ሕዝብ አዋረዳችሁት፡፡ የበላይ ዘለቀ ነን ማለት በነጮች የበላይነት አምኖ በአሽከርነት ቆሞ ማደግደግ አይደለም፡፡ ይህ ትልቁ በአስተሳሰብ የመውረዳችሁ መገለጫ ነው፡፡

ሌላው የመዝቀጣችሁ ትልቁ ማሣያ ከአክራሪ እሥላማዊ ኃይሎች ጋር በመሰለፍ ከጀርባ የግብጽና የሻዕቢያን ፍላጐት ለማሳካት ሀገሪቱ ወደ ብጥብጥና ቀውስ አዙሪት ውስጥ ገብታ ሠላሟ ጠፍቶ ምስቅልቅልዋ እንዲወጣ ወጣቱን ለጥፋት በመማገድና በማነሳሳት የፖለቲካ ሥልጣን እንይዛለን ብላችሁ ማቀዳችሁ ነው፡፡ ጉድ በል ሀገሬ የሚባለው እንደ እናንተ ዓይነት ጉዶች ተፈጥረው ሲገኙ ነው፡፡

ቤተክርስቲያን ለማቃጠል እሥላማዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ለመመሥረት በማቀድ ውስጥ ውስጡን ረዥም ዘመን ሲሰራ ከኖረው የግብፅ ሙሥሊም ብራዘር ሁድ የኢትዮጵያ ቻፕተር ከሆነው ጂሀዳዊ ኃይል ጋር በፍቅር ተሳስራችሁ መቆማችሁ በእናንተ የፖለቲካ ታክቲክ ተደርጎ ቢወሰድም መሠረታዊና ታሪካዊ ግድፈት በመሆኑ በእርግጥም ወርዳችኋል፡፡ ቀን ሲፈቅድላቸው መጀመሪያ ጅሀድ ብለው የሚቀሉት የእናንተኑ አንገት ነው፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ የቀለም አብዮትን በኢትዮጵያ ለማራመድ በምዕራባውያን ኤምባሲዎች እየታገዘና እየተረዳ ተጨማሪ ሥልጠናም እየተሰጠው በርቀትም ከግንቦት ሰባት ጋር ተቀናጅቶ በመሥራት ላይ እንዳለ ይታወቃል፡፡

የእናንተ እምነት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሳይሆን በአሜሪካ ሴኔትና በአውሮፖ ሕብረት በጐ ችሮታ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ አምላኮቻችሁ ቤተ መቅደሳችሁም እነሱው ናቸው፡፡ ውዳሴያችሁም፣ ፀሎታችሁም፣ አቡነ ዘበሰማያት የምታደርሱትም ኒውዮርክና ለንደን ላሉ ነጫጭ ጣኦቶቻችሁ ነው፡፡ እንደዚህ ነው ኢትዮጵያን ለባዕዳን ፍላጎት ማስፈፀሚያ ልትሸጧት የተነሳችሁት፡፡ ይህ መንገዳችሁ ይዘልቅ ወይንም ያዋጣችሁ እንደሆነ አብረን እናየዋለን፡፡

ሌላው የአስተሳሰብ ድህነትና መዝቀጣችሁ መገለጫ ከትናንት ባለመማር አንድ ወጣት ትውልድ ዱላና ደንጊያ፣ ጩቤና ገጀራ ይዞ አደባባይ ይውጣና ይተላለቅ፤ ተነስ! ወጣት ነህ፤ ሙትና አገርህን ነፃ አውጣ፤ አደባባይ ወጥተህ አትመለስ፤ ወዘተ... የሚለው በተለያዩ ሀገራት ለቀለም አብዮት ማካሄጃነት በምዕራባውያን ኃይሎች የተነደፈውን ሥልትና ታክቲክ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ተግባራዊ እናደርጋለን በሚል በዚሁ ሥራ ላይ ለሊት ከቀን ተጠምዳችሁ መባዘናችሁ ነው፡፡

አዬ ጉድ አያ አለ የአባይ ማዶ ሰው! ምስቅልቅልና ሰፊ አስተዋይነትና ጥንቃቄና ትዕግስትን በሚጠይቀው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ እኛ ብቻ ነን ለሀገራችን መፍትሔ ያለን፤ መፍሔውም አመጽና ሁከት መፍጠርና ሥርዓቱን በኃይል ማስወገድ ነው የሚለው ማንቡዋቸር በድሀው ልጅ ደም ለመነገድና በመሰላልነት ለመጠቀም እየሄየዳችሁበት ያለውን የድጥ መንገድ ያሣያል፡፡

በሀገር አማን የጀመራችሁት የመአት አውርድ መክለፍለፍ አገርና ልጆችዋን ይዘን እንጥፋ የሚለው ጥድፊያ የሀገሪቱን ወጣት ኃይል ለማጥፋት ያሴራችሁት ታላቅ ሴራ አንዱ የመዝቀጣችሁ ዋና አመላካች ነው፡፡

እናትም ሆነች ሀገር ያለልጆቿ ወና ባዶ ቤት ማለት ነች፡፡ የእናንተ ሴራ ኢትዮጵያውያን እናቶችን ጥቁር ሸማ ለማልበስ የቀደመው ትውልድ ጥፋት አንሶ ሌላ ዙር የትውልድ ጥፋትና እልቂት ለመፍጠር ነው፡፡

በዚህ ዘመን መነጋገር፣ መወያየት፣ መደማመጥ፣ ልዩነትን አቻችሎ በብልህነትና በአተዋይነት ለጋራ ሀገር መሥራትና መቆም እየተቻለ በደም መፋሰስ ለውጥ ይመጣል ብሎ ማመን እንስሳዊና አረመኔያዊ የወረደ አስተሳሰብ ነው፡፡ ይልቁንስ የተሻለ አስተሳሰብና ዘመነኛ የሚባለው ሀገርም ሳትወድም ልጆቿም ሳይጠፉ ሠላማዊ ለውጥን ማሰብ ነው፡፡

ለምንስ አንድ ሰው ይወድቃል? ለምንስ የሀገሬ ሠላም ይደፈርሳል? ለምንስ እኛ እርስ በእርስ በተባላን ቁጥር ለኢትዮጵያ ጠላቶች የበለጠ በር እንከፍታለን? ሀገሪቷንስ ወደ አዘቅትና ቁልቁለት ወደ ከፋውም ድህነት እንወስዳታለን?

ጥላቻና ቂም በቀል ተያይዞ ከመጠፋፋት በቀር ለሀገርና ለሕዝብ የሚበጅ ምን ትርፍ አለው ብሎ ደግሞና ደጋግሞ ማሰብን ይጠይቃል፡፡ የምንከተለው መንገድ ባይሆንስ ባያዋጣስ የሀገሪቱ ቀጣይ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል? ብሎ ማሰብም ትልቅነት ነው፡፡

ሀገር መውደድና የሀገር ፍቅር የሕዝብ ፍቅር ጥልቅ ስሜት መሆኑ ቢታወቅም ሀገሬንና ሕዝቤን በሥልጣኔና ዘመናዊ አስተሳሰብ ላንፃት ልምራት፣ ሕዝቡ ተከባብሮና ተቻችሎ እንዲኖር ችግሩንም በሠላማዊ ውይይትና በመግባባት እንዲፈታ ላድርግ፣ እናድርግ ብሎ ማሰብ እንጂ በመተላለቅ በመጠፋፋት መፍትሄ ይመጣል ብሎ ማሰብ አስተዋይነትም ትልቅነትም አይደለም፡፡ ሊሆንም አይችልም፡፡

ከምንም በላይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እጅግ በጣም ስስና ውስብስብ በመሆኑ ጥልቅ አስተዋይነትን፣ እርጋታን፣ ከጥላቻ ፖለቲካ መውጣትን፣ ያለንና የደረስንበትን ልማትና እድገትን ይዘን ፖለቲካዊ ውድድሮችን ሠላማዊ መንገድ ብቻ ማካሄድን ይጠይቃል፡፡

ወጣቱንም በጥላቻ ተመርዞ እንዲነሳ ከመቀስቀስ ይልቅ ስለ ሠላም፣ ፍቅር፣ ተከባብሮ በልዩነት መኖርና ባሕልን እንዲያከብር ማስተማር የአዛውንቶችም ሆነ ኢትዮጵያዊ ታላቅ ራዕይ አለን የሚሉ ተቃዋሚ ፖርቲዎችም ቀዳሚ ተግባር መሆን ይገባው ነበር፡፡

ለሀገር እድገት የመጨመር ራዕይን የያዘ በተጀመረው ላይ የበለጠ የሚያሳድግ የሰው ኃይልንና ጉልበትን መፍጠር እንጂ እኛ ካልመራናት፣ እኛ እርካቡን ካልጨበጥን ሁሉም ነገር ይጥፋ፤ ይውደም፤ ሰውም ይለቅ፤ ብሎ በግትርነት በእልህ በበቀል በጥላቻ በሥሜታዊነት ተጠፍንጎ ለሀገር ጥፋት መነሳት ጥልቅ ጥላቻን የሚገልጽና የሚያሳይ ነው፡፡

ይህን ከመሰለው የዘቀጠ አስተሳሰብ ያልተላቀቀና ስክነት በሌላቸው ኮበሌዎች የሚንደቀደቅ ድርጅት ወይንም ግለሰብ የአንድ ወገንን አስተሳሰብ ብቻ ሙጭጭ ብሎ በማቀንቀን ሀገር እመራለሁ ብሎ ቢያስብ መቼውኑም አይሳካለትም፡፡

ሀገር የብዙ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሀይማኖቶች፣ ባሕልና ታሪክ ወዘተ ድምር ዋልታና ምሰሶ ነች፡፡ የሁሉንም እኩል መብት በጋራ በማክበር፤ በአብሮነት ተሳስሮ በደግና በክፋው ዘመን ፀንቶ በመከራና ሀዘን በደስታና ፈንጠዝያው ሁሉን በጋራ ተካፍሎ፤ በህብርም ዘምሮ ፀንቶ ከጥንት እስከ ትናንትና ዛሬ የዘለቀ ሕብረ ቀለም ግን ደግሞ በውል በአንድ መለያ ተለይቶ የሚታወቅ ሕዝብ የሚኖርባት ሀገር እንጂ የእኛ ብቻ አስተሳሰብ የበላይ ነው የሚባልበት አይደለችም፡፡ ይህንን ማጤን አይከፋም፡፡ ከአስተሳሰብ መዳሸቅ፣ ድህነት፣ እንዲያም ሲል መውረድ ይታደጋል፡፡

አልሻባብ በተደጋጋሚ የጀሀድ ጦርነት ባወጀበት፣ ግብጽና ሻዕቢያ ባለ አቅማቸው ግልጽና ግልጽ ባልሆነ አካሄድ እየወጓትና እየተፈታተኗት፤ አነግ ደግሞ ከግብጽ ጋር ተሰልፎ የመገንጠልን ጥያቄ በአዲስ መልክ

እያራገበ ባለበት፣ እሥላም አክራሪዎች በሥውር ሲደራጁ ቆይተው የትጥቅ ችግር ለመጀመር ፍንጭ ባሳዩበትና መረጃም ባለበት በዚህ ወቅት፤ በኢትዮጵያ አመጽና ሁከት በመፍጠር ሀገሪቱን የቀውስ አዙሪት ውስጥ ለመክተት በሠላማዊ ሰልፍ ስምና ሽፋን መንቀሳቀስ ኢትዮጵያንና ህዝቧን ብሄራዊ ህልውናዋን ለማጥፋት የተወጠነ የክፍለ ዘመኑ ታላቅ ሴራ ነው፡፡

በቀጥታ ከውጭ ኃይሎች የገንዘብና የሌላ እርዳታ በመጠቀም ለሀገር ውስጥ ተቃዋሚውና ለግል ጋዜጦችና መጽሔቶች በመስጠት ኢትዮጵያ በአመጽ እንድትናጥ ሕዝቡን እየጐተጐቱ ያሉት እነዚህ ወገኖች በእርግጥ ለሀገሪቱ አሳቢና ተቆርቋሪ ነን ብለው ሲናገሩ አያፍሩም?

መንግሥትን በሠላማዊ መንገድ መንቀፍ፣ መተቸትና መታገል ሙብታቸው ነው፡፡ ግን ደግሞ መንግሥትን ስለጠሉ ብቻ ሀገርና ሕዝብ ይጥፋ፣ ይውደም፣ ይበታተን ማለት አለባቸውን? ኢትዮጵያዊነት ይህ ነውን? ለዚህ ነው አስተሳሰባቸውና አካሄዳቸው ለሀገር ጥፋት ታላቅ አደጋ ስለሆነ ደረጃው የወረደ ነው ያልነው - በእነሱው አባባል በነበላይ ማናዬ አማርኛ፡፡

ማህበራቱን በተመለከተ በላይ ማናዬ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበርንና የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበርን እንኳን በስም ለይቶ ሳያውቅ በስማ በለው ብትሩን ያነሳ ድንገቴ ጋዜጠኛና ኋላም የሰማያዊ ፖርቲ ካድሬ ሆኖ በጭፍን የሚናወዝ በመሆኑ አይፈረድበትም፡፡ ከእሱም ከፖርቲውም ምንም የሚጠበቅ ነገር የለም፡፡

ትውልድ እንዲተላለቅ፤ ደም እንዲፋሰስ ዱላና ስለት ይዘህ ውጣ ብለው በጋዜጣቸው የሩዋንዳን እልቂት ዓይነት ጥሪ ካስተላለፉ ግን ሰሚ ካጡ ደም ናፋቂ ቦረንትቻዎች ከቶስ ምን መጠበቅ ይቻላል?

ወጣትና አፍላ ሕፃናትን በጭፍን ጥላቻ ስሜት እየኮተኮተና እያጠመቀ፤ በፌስ ቡክና በየዌብሣይቱ የከፋ ጥላቻን በጦማርያኑ አማካይነት ሲያሰራጭ የነበረው ሰማያዊ ፖርቲ፣ አንድነትና ግንቦት ሰባት በግል ጋዜጠኝነት ስም ያሰማሯቸውና የከፈቷቸው መጽሔቶችና ጋዜጦች ለቅስቀሳ ሥራው የሚጠቀሙባቸው በገንዘብ የሚያግዟቸው እንደሆኑ በይፋ ከታወቀ ውሎ አድሯል፡፡

ሙያውን ማርከስና ማብከትም የተካሄደውና የተፈፀመው በነዚሁ ፖርቲዎች አማካይነት ነው፡፡ ከትናንት እስከ ዛሬ ሁሉም ተቃዋሚ ፖርቲዎች በአገር ውስጥና በውጭ ያለው በግሉ ፕሬስ ውስጥ በሽፋን የሚሰሩ ጋዜጦችና መጽሄቶች ነበሯቸው፤ መጥቀስም ይቻላል፡፡ ስለዚህም የጋዜጠኞች ማህበራቱ ሳይሆኑ የወረደውና የዘቀጠው ራሱ ሰማያዊ ፖርቲ ነው፡፡

ማህበራቱ ጋዜጠኛ ላልሆኑ ግለሰቦች፤ ሆነው የሚታወቁ ግን ደግሞ ከሙያው ጋር ባልተያያዘ ሌላ ድርጊት ለታሰሩት ድምጽ ማሰማት አይችልም፡፡ እንበልና ኢንጂነር ይልቃል ከፖርቲያቸው መርህና ደንብ ውጪ በማታለልና በማጭበርበር በሌብነት ወንጀል እጅ ከፍንጅ ተይዘው ወይንም በሌላ ወንጀል ቢታሰሩ ሰማያዊ ፖርቲ ድምጽ ያሰማ ይሆን? በእርግጠኝነት አያሰማም፡፡ መስመሩ አይገናኝምና፡፡

በቅርብ ቀን ተቋቁሞ ጫና ደረሰበት፤ ማህበራቱም አዋከቡት የተባለው የጋዜጠኞች መድረክ የተባለ የጋዜጠኛ ማህበር የተቋቋመው የነሰማያዊ ፖርቲና የግንቦት ሰባትን ዓላማን ለማራመድና በሥራ ላይ በግል ጋዜጠኝነት ስም ያሰማሯቸው ካድሬዎቻቸው ሲታሰሩና በሕግ ሲጠየቁ ለምዕራባውያን ጌቶቻቸው ድምጽ በማሰማት ዓለም አቀፍ ጩኸት እንዲፈጥሩ መሆኑን እነሱው አቅደው የሰሩት በመሆኑ መደነቋቆሩ ምንይረባል? ስታውቂው ማዘንጊያ አሉ አለቃ ገብረ ሀና?

ምን ያለበት ዝላይ አይችልም ሆነና ገና በምሥረታ ላይ እያለ ሁለትና ሦስት ወራት ሳይሞላው የማህበሩ ሊቀ መንበርና ምክትል ሊቀመንበር ለስብሰባ በሄዱበት ሀገር ኮበለሉ ጥገኝነት ጠየቁ ይለናል የነገረ ኢትዮጵያው ልሣን አንዱ አዘጋጅ በላይነህ ማናዬ በልብ አድርጉ አምዱ፡፡

በላይ ማናዬን ጨምሮ የጋዜጠኞች መድረክ ስብስብ በኢትዮጵያ የግሉ ፕሬስ ውስጥ ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ የሚባሉ ዓይነት ናቸው፡፡ ባልኖሩበት፣ ባላሳለፉበት፣ ባልሰሩበት ታሪክና ውጣ ውረድ ውስጥ ደርሰው ራሳቸውን ከጣራ በላይ ቆልለው ሊጃጃሉ ይከጅላቸዋል፡፡

ጀግና ነን ለሀገር ለፕሬስ ነፃነት ተቆርቋሪ፤ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብት ተሟጋች ወዘተ...እያሉ እምቡር እምቡር ይላሉ፡፡ ራሳቸውን ታልቅ ምሁርና ፈላስፋ አድርገው በባዶ ሜዳ ይንከላወሳሉ፡፡

በየሰልፉ ጃሎ የሚሉና የሚያቅራሩ የአልተገራና መረን አስተሳሰብን በጀርባቸው አዝለው የሚያሸበሽቡ ናቸው፡፡ ይህ ነው የአስተሳሰብ መውረድና  ብሎም መንኮታኮት፡፡ ሌሎችን እነዚሁ ጨለምተኞቹ "ጨለምተኛ" እያሉ ስም መለጣጠፍ፣ ማጥላላት፣ መልካም ስማቸውንም ጥላሸት መቀባባት፡፡